# እጅግ አሳዛኝ ዜና

- የዲሞግራፊው ቅየራ አዲስ አበባ መገናኛ ብዙሃን ውስጥ ገብቷል
- 86 የአዲስ ቴሌቪዥን ሰራተኞች ተባረሩ
- 70 የሚሆኑት እጅግ ከደረጃ በታች ተመድበዋል

#ነገሩ_እንዲህ_ነው
በቅርቡ አዲስ የስራ ደረጃ ድልድል መመሪያ በሚል ሰበብ መስፈርቱ እጅግ ከባድ(ማንም ሊያሟላው የማይችል) ፎርም በማዘጋጀት እንዲሞሉ ይደረጋል : ይሁንና የሚፈልጓቸውን ሰዎች ባታሟሉም አሟላለሁ በሚል ሙሉት በሚል በሚስጥር ተነግሯቸዋል::

ቀሪዎቹ ግን ሳይሞሉ በማለፋቸው #ተንሳፋችኃል ወይም የስራ መደብ አልተገኘላችሁም በሚል 155 የሚደርሱ ሰራተኞች ይታገዳሉ:: ከነዚህ ውስጥ 75 ካካባቢ የሚሆኑት ባንፃራዊነት በነበራቸው የቀደምት ፖለቲካዊ ተሳትፎ(ተለጣፊነት ) እና ተገቢ ሂደት ጠብቀው መብታቸውን ሲጠይቁ ይህን ቡድን ከ2 እንክፈለው በሚል ምክንያት #አንጥላቸውም በሚል ከደረጃ 15 እና 16 ወደ ደረጃ 6 እና 7 ማለትም ከአስተባባሪነት እና አርታኢነት ወደ ጀማሪ እና ሪፖርተር 1 መደብ ተመድበዋል ( ይሄውም በኛ በጎ ፈቃድ ነው ) በሚል:: ቀሪዎቹ ግን #መውደቂያችሁን_ፈልጉ ተብለዋል::

- መመሪያው ግን ከ3 ደረጃ ዝቅ ብሎ መመደብ አይችልም : ይንሳፈፋል የሚል ቢሆንም በራሳቸው ይሁንታ ግን እስከ 6 ደረጃ ዝቅ አድርገው መድበዋል::

በሌላ በኩል አዲሱ መመሪያ 873 የሰው ሃይል ያስፈልጋል የሚል ሲሆን ተቋሙ ያለው ግን 530 ሰራተኞች ብቻ ናቸው : ያ ማለት ትርፍ የሰው ሃይል ያለውን መደብ ለሚፈልጉት ሰው አስቀምጠዋል ማለት ነው ብለዋል::

#ነገሩ_ይቀጥላል
ጭብጥ ነገሩ ወዲህ ነው : ከነዚህ ሰራተኞች ውስጥ በጣም ጥቂት የሚባሉት ኦሮሞ ሆነው አክራሪ ብሄርተኝነቱ ላይ የሌሉበት እና ስራቸውን በትክክል እየሞገቱ የሚሰሩ ሲሆኑ ቀሪዎቹ ግን አማራ እና ሌሎች ናቸው : በአንፃሩ ግን ተቋሙን ለመለወጥ አዲስ ሰው ያስፈልገናል በሚል  አዲስ ሰራተኞ ለማስገባት ቀደም ሲል አመራሮች ተናግረው ነበር ነው ያሉት::

#ማሳያዎቹም
- የተባረሩት ብዙዎቹ ባለሙያዎች ሾፌሮችን ጨምሮ በ2ኛው ዙር የህልውና ዘመቻ የተሳተፉና እውቅና የተሰጣቸው ሲሆኑ አብዛኞቹ በዚህ የማባረር ፕሮጀክት የተካተቱ ናቸው ( ዘመቻውን የተሳተፉት ለሀገር ሳይሆን ለብሄራቸው ሲሉ ነው በሚል ቀደም ሲል ያስወሩ ነበር)

-ጀማሪ የስራ ልምድ ያላት ልጅ በተቋሙ የእንግሊዝኛ ክፍል አስተባባሪ/ዳይሬክተር ሆና ተመድባለች
- 2 አመት በምክትል ዋና አዘጋጅነት የሰራ ዳይሬክተር ይሆናል የሚለው መመሪያ በመጣስ ከፍተኛ ሪፖርተር የነበረ የትግርኛ ክፍል ዳይሬክተር አድርገው ሹመዋል::
- ምክትል አዘጋጅ ለመሆን 2 አመት በከፍተኛ አርታኢ የሰራ ቢልም ያልሆነን ሰው መድበዋል::

- ይህን ሁሉ አቤቱታ ይዘው ፐብሊክ ሰርቪስ ቢሮ : የከተማው ምክር ቤት የሚዲያ ዘርፍ ቋሚ ኮሚቴ እና የተቋሙ ቦርድ ድረስ ቢሄዱም የተሰጣቸው ምላሽ ተመሳሳይ መሆኑን እና ማስጠንቀቂያ ድረስ

መሰጠታቸውን ሰምተናል::

#ሌላው_የሚገርመው
ይህን ሁሉ አቤቱታ በማስተባበር የሚጠይቁትን ለማሸማቀቅ በሚል አንድ ማስታወቂያ የወጣ ሲሆን "በተቋሙ ውስጥ ህገወጥ ድርጊት ለመፈፀም የምትንቀሳቀሱ ሰራተኞች ከድርጊታችሁ እንድትታቀቡ እያሳሰብን ይህን ባታደርጉ ካስተዳደራዊ ርምጃ ባለፈ ከፀጥታ አካላት ጋር በመነጋገር ህጋዊ እርምጃ እንወስድባችኃለን" ይላል::

#ዛሬም ይህንን በይፋ ጀምረው ከነዚህ ውስጥ የተወሰኑት ላይ በህግ አግባብ ሳይሆን በምሽት ወደቤታቸው ሲገቡ #ዱርየ ሊባሉ በሚችል ደረጃ ተሸከርካሪን በመጠቀም አግተው "ከዚህ በኃላ በዚህ ጉዳይ ብትገባ እንገልሀለን : አርፈህ ልጅህን አሳድግ" በሚል አስፈራርተውና ስልካቸውን ሰብረው ለቀዋቸዋል::

#በነገራችን_ላይ
ስራ አስኪያጁ አቶ በቀለ ሙለታ ከዚህ ቀደም በኢዜአ : ዋልታ እና ፋና ቴቪ እጅግ በጣም መጥፎ ስራ (ለመግለፅ የሚከብድ) በመስራትና ሰራተኛን በማሰቃየት  እየተቀያየረ የቆየ እና ከስራ ተባሮ 5 ወር አካባቢ ያለስራ ቆይቶ ለአ.አ መገናኛ ብዙሃን የተመደበ ነው::

ከአመት በፊት በፍትህ መፅሄት ስለተቋሙ  ወጥቶ በነበረው ዘገባ ችግር ሲል የጠቀሰው የተቋሙ ምክትል ዳይሬክተር የነበሩት እና አማራ ጠል አመለካከት ያለው አቶ ሳሙኤል ከበደም ዋና ተዋናይ መሆናቸውንም ገልፀውልኛል::

አስፈላጊ ከሆነና ችግሩ ካልተስተካከለ ነገሩን በመጋፋጥ በምስል ቃለምልልስ እንደሚሰጡም ነው ባለሙያዎቹ የገለፁት::

አራጋው ሲሳይ